# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የዘመነ ጽጌ ስድስተኛ ሳምንት

በዚህ ዕለት ሰማይን በከዋክብት ያደመቀ የተጋረደበትን ደመና ያራቀ የምድር ተክሎችን አዝዕርትን በአበባ በፍሬ ያሸበረቀ መሆኑን እያሰበች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን ታመሰግናለች።

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ጸገየ ወይን ወፈርየ ሮማን
ወፈረዩ ኵሉ ዕፀመ ገዳም
(ወይን አበበ ሮማን እና የዱር አበቦች ደግሞ አፈሩ) የሚል ነው።

### የዕለቱ ምስባክ

ዐፀደ ወይን አፍለስከ እምግብፅ
ሰደድከ አሕዛብ ወተከልከ ኪያሃ
ወጼህከ ፍኖተ ቅድሜሃ

ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣህ (አፈለስክ)
አሕዛብን አባረርክ እርሷን ተከልክ
በፊቷም ሥፍራን (መንገድን) አዘጋጀህ (ጠረግህ)

መዝሙር ፸፱፥፰

<u>ትርጉም (ምሥጢር)</u>
የወይን ተክልን (እስራኤል) ከግብጽ አወጣህ። አሕዛብን ከከነዓን አውጥተህ የደረሰ መከራቸውን የታነጸ ግንባቸውን ለእስራኤል አውርሰህ በከንዓን ተከልካቸው። ቀን በደመና ሌሊት በብርሃን እሳት እየመራህ ሲዋጉ አሕዛብን እየመታህ መንገዱን አቀናህላት ማለት ነው።

**ወንጌል፥** ማቴ ፳፩፥፴፫ እስከ ፍጻሜ ይነበባል።
**ቅዳሴ፥** ጐሥዐ (ቅዳሴ ማርያም)

ቅዳሴው ያልተለወዋወጠው የህጻኑንና የእናቱ ስደት የሚታሰብበት በመሆኑ እና ቅዳሴው በስተመጨረሻው ይህንኑ የሚያስታውስ ኃይለ ቃል ስላለው ነው።

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፲፩፥፲፫-፳፭ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ራእይ ፲፪፥፲፫ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋርያት ሥራ ፲፩፥፩-፲፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

### አስግሩ ለነ ቆናጽለ ንዑሳነ
### እለያማስኑ ዐፀደ ወይንነ
### የወይን ተክል (ጓሮ) የሚያጠፉትን ቀበሮዎች አጥምዱልን
(መኃል ፪፥፲፭)

ወይን በክረምት የሚደክም በበጋ የሚያብብ ተክል ነው። የወይን ተክል ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያሻው በመሆኑም ምንም እንዳይደርስበት ዙሪያውን ታጥሮ ተቀጥሮ በተጨማሪም የሚጠብቀው ሰው በግንብ ተቀምጦ በቅርብ ይከታተለዋል (ኢሳ ፭፥፳ ። ማር ፲፪፥፩) ሐረጉም እንዳይሰበር መደገፊያ ይሠራለታል (ሕዝ ፲፯፥፯)። የበለጠ እየሰፋና እየጠነከረ እንዲያፈራም በየዓመቱ መገረዝ አለበት (ዘሌ ፳፭፥፲፫)። በወይን ተክል ታዲያ ቀበሮዎችና ተኩላዎች እንዳይደርሱበት መደረግ ነበረበት። የሚያስቸግሩ ቆናጽል (ቀበሮዎች) ካሉም በወጥመድ ተይዘው መገደል ነበረባቸው። የቀበሮዎቹ ኮቴም ሆነ እስትንፋስ ለወይኑ ጠንቅ በመሆኑ ቀበሮዎቹ ይጠመዳሉ።

ይህ ወይን የቤተ ክርስቲያንና የቤተ እስራኤል ምሳሌ ሆኖ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሷል። ለምሳሌ ዛሬ በተነበበው ወንጌል ላይ የተጠቀሰው ወይን የቤተ እስራኤል (የሕዝበ እስራኤል) ምሳሌ ሲሆን ቅጥሩ የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ገበሬዎቹ ደግሞ ሕዝበ እስራኤልን እንዲያገለግሉ የተመደቡ የአይሁድ ሥጋውያንና መንፈሳውያን መሪዎች ሲሆኑ የወይን ፍሬ እንዲያመጡ ከአንድ እስከ ሁለት ጊዜ የተላኩት ባሮች ደግሞ ዓበይትና ደቂቀ ነብያት ናቸው። መጨረሻ ላይ የተላከው የወይኑ ጌታ ልጅ ደግሞ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ከዐፀደ ወይኑ አውጥተው መግደላቸው በቀራንዮ ከከተማ ውጭ ተሰቅሎ ስለ ሕዝቡ የመሞቱ ምሳሌ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪ (ኢሳ ፭፥፩-፭ ። ሉቃ ፳፥፱-፲፰) ያለውን ብናነብ ስለ ወይኑ ትርጉም በሚገባ ለማወቅ እንችላለን። የዕለቱ ወንጌል የሃይማኖት መሪዎች ሕዝቡን ከአምላኩ እንደለዩት ፍሬውንም እነርሱ እንደበሉት ሲናገር የኢሳይያስ ትንቢት ደግሞ ወይኑ ጭራሹን በጐ ፍሬ (ፍርድና ምሕረት) የማያፈራ (የሌለው) መሆኑን ያስተምረናል። መድኃኒታችን የሕይወታችን መሰረት በመሆኑ በወይን ግንድ ሲመሰል ቤተ ክርስቲያን በቅርንጫፍ ተመስላ በወንጌል ተገልጻለች (ዮሐ ፲፭፥፩-፲፭)።

ቅርንጫፉ ከወይን ግንድ ሳይለይ እንዲኖር ቅርንጫፉን ከወይን ግንድ የሚለዩ ቀበሮዎች የወይኑን ፍሬ የማይሰጡ ለራሳቸው የሚውጡ የሰው አውሬዎችን እንዲያጠምድልን እንደ ሰለሞን ወደ እግዚአብሔር ልንለምን ይገባል። ስንቱ ለእግዚአብሔር ተክለ ፍሬ ለባለቤቱ ሳይደርስ ቀርቷል። ስንቱስ የወይን ሐረግ ተረግጦና ተሰባብሮ ይታያል። ክርስቲያን ሆይ ከወይኑ ግንድ ከአምላክህ ከኢየሱስ ክርስቶስ እንዳትለይ በጸሎት ትጋ። በቀበሮ የተመሰሉት የሐሰት የኑፋቄ መምህራን ናቸው። እነርሱ ሰውን ከአምላኩ ሊለዩት ስለሚችሉ ልንርቃቸው ይገባል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር .... አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ
EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM